ኑሩ ሙሐመድ
(ክፍል አንድ)
========
የውበት ገፅታ
========
ሲኸልቃቸው ዘይኖ ነው። የውበት መለኪያ፣ የልብ መነጠቂያ አድርጎ ተክለ-ሰውነታቸውን አበጅቶታል። ያያቸው ከ`ራሱ ላይሆን በውበታቸው ይወሰዳል፤ ይማረካል።

ሁሉን አድራጊው በምርጥ ፀባይ ሸለማቸው። የመልካም ነገር ሁሉ መሰብሰቢያ፣ የላቁ ስብዕናዎች መገኛ ሆነዋልና ለታካች ነፍሶች ማረፊያ ይሆኑ ዘንድ ላካቸው።

የአካላዊም ሆነ የጠባይ ውበት ሁሉ መገኛ ናቸውና ያወጉት ሁሉ ወደቀልብ ይዘምታል። አብረውት ሆነው የሚናፍቅ ሷሂብ ከበባቸው። የተመለከቷቸው ሁሉ "አምሳያቸውን አይቼ አላውቅም!" ይላሉ።

በጤፍ ቁንዳላ ውስጥ ከተቋጠሩ ፍሬዎች ቁጥር በላይ

የአላህ ሰላም ይስፈንባቸውና በጠባዬ ሰናይነቱ ወደር የሚሆን አልተፈጠረም!! አይፈጠርምም!!

በራእ ኢብኑ ዓዚብ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዲህ ይላሉ: - «ነቢዩ [ﷺ] ከሰዎች የበለጠ ፊታቸው የተዋበ፣ ፀባያቸውም ከሁሉ ያማረ ናቸው። የገነነ 'ረዥም አይደሉም፤ አጭርም አይደሉም።» ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

አሚሩል-ሙእሚኒን ዐሊይ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንዲህ ገልፀዋቸዋል: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] አጭርም 'ረዥምም አይደሉም። ጭንቅላተ-ትልቅ ናቸው። መዳፍና እግራቸው ደንዳና እና አጠር ያለ ነው። ፊታቸው ቅላት የጠጣ ነጭ ነው። የሆዳቸው ፀጉር ረዥም ነው። ሲራመዱ ከቋጥኝ ላይ የሚንደረደሩ ይመስላል። ከርሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ አምሳላቸውን አይቼ አላውቅም።» ኢማም አሕመድ ዘግበውታል።

ዐሊይ [ረዲየላሁ ዐንሁ] የአላህ መልክተኛን [ﷺ] ሲገልፁ እንዲህ ይላሉ: - «የአላህ መልዕክተኛ [ﷺ] የተጋነነ 'ረዥም ወይም አካላቱ የተቀላቀለ አጭር

አልነበሩም። ከሰዎች መሀል መካከለኛ የሚባሉ ነበሩ። ፀጉራቸው ከርዳዳ አልነበረም፤ በጣም ስስም (እንደ ዝንጀሮ ፀጉር) አልነበረም። ጠንካራ ሆኖ ሉጫ ነበር። ጉንጫቸው ስርጉድ አይደለም። አባጣ ሆኖ ጉንጫም አልነበሩም። ፊታቸው ክብነት ነበረው። ነጭ ናቸው፤ ቅላት የጠጣ ነጭ። ብሌናቸው ከስፋቱ ጋር በጣም ጥቁር ነው። ሽፋሽፍታቸው 'ረዥም ነው። የመገጣጠሚያ አጥንቶቻቸው ትልቅ ናቸው። ከትከሻ እስከ ወገባቸው ያለው ክፍል ግዙፍ ነው። የሆድ ፀጉር አላቸው። መዳፍና እግራቸው ወፍራም ነው። ሲራመዱ ከዳገት ላይ የሚንደረደሩ ይመስላል። ወደ ኋላ ሲዞሩ በሙሉ አካላቸው ይዞሩ ነበር። በትከሻዎቻቸው መካከል የነቢያት ማህተም አለ። መዳፈ-እርጥብ፣ ልበ-ሰፊ፣ ልሳነ-እውነት፣ ጠባየ-ልስልስ፣ በመልካም ተዳዳሪ ነበሩ። በድንገት ያያቸው ይፈራቸዋል። ተዋውቋቸው አብሯቸው የኖረ ያፈቅራቸዋል። የገለፃቸው ሰው እንዲህ ይላል: - «ከርሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ እርሳቸው የመሰለን ሰው አላየሁም!»

ኑሩ ሙሐመድ
(ክፍል ሁለት)
==========
የኡሙ መዕበድ ገለፃ
==========
ከመስለሚ በፊት ነው ያየቻቸው፤ ያውም ለጥቂት ሰዓታት። መብልና መጠጥ ፍለጋ ከቀየዋ እግረመንገዳቸውን ጎራ ብለው ነበር። የቃላት ልውውጣቸው ጥቂት ነው!
ኡሙ መዕበድ አስደናቂ ናት! አብሮ የከረመ እንኳን እንደርሷ አይገልፅም! አስተውሎቷ ገራሚ ነው።...
በሌላ በኩል የተፈቃሪያችን [ﷺ] ገፅታ የወገገ፣ ዐይነ-ግቡ፣ በህሊና የሚያድር፣ አይረሴ እና ከማንም የተለየ እንደነበረ በሚገባ እናስምር!

በይሀቂይ እና ሌሎችም እንደዘገቡት: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ከመካ ወደ መዲና ሂጅራ ያደረጉ ጊዜ አቡበክር፣ ሲዲቁ ነፃ ያደረጓቸው ባርያ -ዓሚር ኢብኑ ፉሀይራ- እና የመንገድ መሪያቸው ዐብዱላህ ኢብኑ ኡረይቂጥ አል-ለይሲይ አብረዋቸው ነበሩ።
በመንገዳቸው በኡሙ መዕበድ ዓቲካ ቢንት ኻሊድ አል-

ኹዛዒያ ድንኳን በኩል አለፉ።

አረጋዊዋ ኡሙ መዕበድ በጣም የተከበረች፣ ቁጥብ እና ጠንካራ ሴት ነበሩ። ጉልበታቸውን አጣምረው በድንኳናቸው በር ላይ ይቀመጣሉ። በመንገድ የሚያልፍ ሰውን ያበላሉ፣ ያጠጣሉ።

መንገደኞቹ የሚሸጥ ስጋ ወይም ወተት እንዳላት ጠየቁ። ምንም አላገኙም። ባልቴቷም «ወላሂ እኛ ዘንድ አንዳች ነገር ቢኖር እንድትገዙ አንጠብቅም። በራሳችን ወጪ እናስተናግዳችሁ ነበር። ነገርግን ሰዎች ድርቅ አጋጥሟቸው ረሀብ ላይ ናቸው!» በማለት በደግነት ስሜት አወራቻቸው።

የአላህ መልክተኛ [ﷺ] በድንኳኗ አንድ ጎን አንዲት ፍየል ተመለከቱ። «ኡሙ መዕበድ ሆይ! ይች ፍየል ምንድን ናት?!» አሉ።
«ይችማ በረሀብ ተዳክማ ከሌሎች ፍየሎች ተለይታ ከግጦሽ የቀረች ናት።» አለች።
«ወተት አላት?» አሏት።
«እረ አይኖራትም። የደከመችኮ ናት!» መለሰች።

«እንዳልባት ትፈቅጂልኛለሽ?» በማለት ጠየቋት።
«የሚታለብ ወተት የምታገኝበት ከሆነ ሞክር!» አለች።
በሌላ ዘገባ: - «አዎን! እናትና አባቴ ፊዳ ይሁኑልህና የሚታለብ ወተት አገኛለሁ ካልክ ሞክር!» አለች።

የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ፍየሏን አስጠግተው ዳበሷት። የአላህን ስም ዘከሩ፤ ጡቷን ዳበሷት። ከዚያም ዐስር ሰዎች ገደማ የሚያጠግብ እቃ እንዲቀርብላቸው አዘዙ። እግሮቿን ከፈተች። ወተቷ ተንቧቧ፤ በብዛት መፍሰስ ጀመረ። እቃውም ሞላ።
ኡሙ መዕበድ ጠጣች። ባልደረቦቻቸውን አጠገቡ። ጓደኞቻቸው ደጋግመው ጠጡ። ሁሉም እስከሚበቃቸው ጨለጡ።
ከሁሉም መጨረሻ የጠጡት የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ናቸው። «የሰዎች አጠጪ (ቀጂ) መጨረሻ ነው የሚጠጣው!» አሉ።

ከዚያም በድጋሚ አለቡ። እንደመጀመሪያው እቃውን ሞልተውላት «ይህንን አቡ መዕበድ ሲመጣ አቅርቢለት።» በማለት እርሷ ዘንድ ትተውት ሄዱ።

ብዙም ሳይቆይ ባሏ አቡ መዕበድ በድካም እየተናጠቡ የሚራመዱ ከሲታ ፍየሎቹን እየነዳ መጣ። ወዝ የላቸውም።
እቤቱ ውስጥ ወተት ሲያይ ተደነቀ። «ይህ ወተት ከየት መጣላችሁ! እቤት ውስጥ የሚታለብ ወተት የለ ?! ፍየሎቻችንም ለግጦሽ ርቀው ሄደዋል!» አለ።
«ወላሂ ማንም አላመጣልንም። ነገርግን አንድ የተባረከ ሰው በዚህ አልፏል።» በማለት የሆነውን ሁሉ ተረከች።

ባሏ «ምን እንደሚመስል ግለጭልኝ?!» አላት።
እንዲህ በማለት መግለፅ ጀመረች: -
«የፈካ ውበት ያለው ሰው አይቻለሁ። ተክለ-ሰውነቱ ያምራል። ፊቱ ውብ ነው። ቦርጭ አላነወረውም። የጭንቅላት ማነስ አላጓደለውም። የሚወደድ ቆንጆ ነው። የዐይኑ ብሌን ጥቁር ነው። ሽፋሽፍቱ ብዙና ረዥም፣ ቅንድቡ ጥቅጥቅ ነው። ድምጹ የሚነዝር ቅላጼ ያለው ጎርናና ነው። ዐይኑ ደግሞ ጥቁሩ በጣም የጠቆረ ነጩም በጣም የነጣ ነው። ዐይነ-ኩሌ ነው። ቅንድቡ ቀጭን ነው፤ ሁለቱ ቅንድቦቹ ተገጣጥመዋል። አንገተ-ረዥም ነው። ጺሙ ጥቅጥቅ ነው።

ዝም ሲል ስክነት ይላበሳል። ሲናገር አንገቱ ይቃናል፤ ግርማውን ይለብሳል። ንግግሩ ጣፋጭ ነው። ወሬው መካከለኛ ነው። ትንሽም አይደለም፤ ብዙም አይደለም። ቃላቱ የተለያዩ ቀለማት ያሉት የተደረደረ ሀብል ይመስላል፤ ከተበጠሰ እንደሚበተን።

ከሩቅ ሲታይ ግርማው እጅግ የሚያስፈራ፣ ከቅርብ ደግሞ በጣም የሚያምር ሰው ነው። ቁመቱ መካከለኛ ነው። ከመርዘሙ ብዛት ለዐይን አያስጠላም። ከማጠሩም ብዛት በንቄት አይታይም። በሁለት ቀንዘሎች መሀል እንዳለ ቀንዘል አስበው (ሁለቱ ቀንዘሎች ባልደረቦቻቸው ናቸው።)፤ ከሦስቱ ለተመልካች እጅግ የተዋበው እርሱ ነው።

ዙርያውን የሚከቡ ጓደኞች አሉት። ከተናገረ ያደምጡታል። ካዘዘ ትእዛዙን ለመፈፀም ይሽቀዳደማሉ። በባልደረቦቹ የተከበረ፣ አጀቡ የበዛ ሰው ነው። ጨፍጋጋ ወይም ቂላቂል አይደለም።»
ባሏ አቡ መዕበድ እንዲህ አለ: - «ይህማ ወላሂ ቁረይሾች የሚያሳድዱት ሰውዬ ነው። ብንገጣጠም ኖሮ ልከተለው እፈልግ ነበር!»

ከዚያም ኡሙ መዕበድ ከባሏ ጋር ወደ መዲና ተሰዳለች። ሁለቱም ሰልመዋል።»

ኑሩ ሙሐመድ
[ክፍል ሦስት]
==========
የበድር ጨረቃ
==========
ፊታቸውን ለብቻው እንቃኘው።...
እጅግ የተዋበ ነው፤ አንጸባራቂ ብርሃን የተላበሰ።
የገለጿቸው ሶሐቦች በሙሉ የወገገ ፊት እንደነበራቸው
ያለ ልዩነት ይመሰክራሉ። የሚያንጸባርቅ ገፅታ፤
የሚያስደምም ብርሃን ያለው፤ የሚንቦገቦግ፤ ጎልቶ
የሚታይ ፍካት!...

አንዳንዶቹ የብርሃናቸውን አምሳል ሲጠቅሱ ከፀሃይ ጋር
አዛምደው ነው። ሌሎቹ በጨረቃ አመሳስለውታል።
አንዳንዶች ከጨረቃ ብርሃን ጋር አነጻጽረውታል።
የሁሉም አገላለፅ የፊታቸው አንፀባራቂነት ጉልህ
እንደነበር፣ አስደናቂ ብርሃን የተላበሰ ገፅታ
እንደነበራቸው ያስረዳል።

ተከታዮቹን ሐዲሶች እንመልከት: -

ቲርሚዚ እንደዘገቡት አቡሁረይራ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንዲህ ብለዋል: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] የሚወዳደር ውብ አይቼ አላውቅም። በፊታቸው ላይ ፀሀይ የምትንቀሳቀስ ይመስላል።»

አቡ ዑበይዳ ኢብኑ ዐማር ኢብኑ ያሲር እንዲህ ይላሉ: - «ሩበይ-ዩዕ ቢንት ሙዐው-ዊዝን [ረዲየላሁ ዐንሃ] የአላህ መልክተኛን [ﷺ] ግለጪልን በማለት ጠየቅኳቸው። እንዲህ አሉ: - «ልጄ ሆይ! እርሳቸውን ካየህ ፀሀይን እንዳየህ ነው!» ቲርሚዚ፣ በይሀቂይ እና ሌሎችም ዘግበውታል።

ቲርሚዚ ሂንድ ኢብኑ አቢ ሃላን [ረዲየላሁ ዐንሁ] በመጥቀስ ከሐሰን ኢብኑ ዐሊይ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንደዘገቡት:- «የሹሜዬን (የእናቴን ወንድም) ሂንድ ኢብኑ ሃላን የአላህ መልክተኛን [ﷺ] እንዲገልፁልኝ ጠየቅኳቸው። ነገሮችን አሳምሮ የመግለፅ ችሎታ ስለነበራቸው አጥብቄ በምይዘው መልኩ እንዲገልፁልኝ ተመኝቼ ነበር። እንዲህ አሉኝ: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] እጅግ የተከበሩ ታላቅና ባለግርማ ነበሩ። ፊታቸው እንደ በድር ጨረቃ (ሙሉ

ጨረቃ) የሚያበራ ነበር።»

ከጃቢር ኢብኑ ሰሙራ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንዲህ ይላሉ: - «የአላህን መልክተኛ [ﷺ] ሙሉ ጨረቃ ባለችበት ሌት ሙሉ ቀይ ለብሰው አየኋቸው። ተራበተራ አንዴ እርሳቸውን መልሼ ደግሞ ጨረቃዋን ማየት ጀመርኩ። በአላህ እምላለሁ እርሳቸው ከጨረቃዋ የበለጠ የተዋቡ ናቸው።» ቲርሚዚ ዘግበውታል።

ከአቡ ኢስሐቅ አስ-ሰቢዒይ እንደተዘገበው: - «አንድ ሰው በራእ ኢብኑ ዓዚብን የአላህ መልክተኛን [ﷺ] ገፅታ ጠየቃቸው፤ «እንደ ሰይፍ ያንፀባርቅ ነበር?» በማለት። በራእ [ረዲየላሁ ዐንሁ] «የለም! እንደ ጨረቃ ያበራ ነበር!» በማለት መለሱ።» ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

በተመሳሳይ ጃቢር [ረዲየላሁ ዐንሁ] «እንደ ሰይፍ ያንፀባርቅ ነበር?» በማለት ተጠይቀው «የለም! እንደ ፀሀይ እና እንደጨረቃ ያበራ ነበር። ፊታቸው ክብ ነበር።» በማለት መልሰዋል።» ሙስሊም ዘግበውታል።

ቡኻሪና ሙስሊም ከከዕብ ኢብኑ ማሊክ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንደዘገቡት እንዲህ ብለዋል: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ሲደሰቱ ፊታቸው ያበራል፤ የጨረቃ ቁራጭ ይመስል ነበር።»

በይሀቂይ ከአቡ ኢስሐቅ አል-ሀምዳኒይ "ከሀምዳን" የመጣች አንዲት ሴትን በመጥቀስ እንደዘገቡት፤ እንዲህ ብላለች: - «ከአላህ መልክተኛ [ﷺ] ጋር በተደጋጋሚ ሐጅ (ዑምራ ማለቷ ይሆናል?!) አድርጌያለሁ። ግመል እየጋለቡ በከዕባ ላይ ጠዋፍ ሲያደርጉ አይቻለሁ። በእጃቸው ከዘራ ይዘው፣ ሁለት ቀይ መጎናፀፊያዎችን ለብሰው ነበር። ፀጉራቸው ትከሻቸውን ሊነካ የቀረበ ነው። በጥቁሩ ድንጋይ አጠገብ ሲያልፉ በከዘራቸው ይነኩትና ከዘራቸውን ይስሙት ነበር።»
አቡ ኢስሐቅ (የሐዲሱ ዘጋቢ) እንዲህ ይላሉ: - «መልካቸውን ግለጪልን!» አልኳት። እንዲህ አለች: - «እንደ በድር ጨረቃ ነው። ከርሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ እርሳቸውን የመሰለ አላየሁም።»

መዲና ሲገቡ የተዜመውን አንረሳም! "ጦለዐል በድሩ

ዐለይና!"... "የበድር ጨረቃው መጣልን" ማለት ነው!

አንጸባራቂው የፊታቸው ገፅታ የስብዕና ምልኣትን የሚጠቁም ምልክትም አለው። የበርካታ ምስጢራት መካን እንደሆነም ይሳበቅበታል። እንደውም በእርግጥ የአላህ መልክተኛ ለመሆናቸው አሳማኝ መረጃም ነበር!...
አላጋነንኩም!...
ዐብዱላህ ኢብኑ ሰላም የተናገሩትን ነው ያሰፈርኩት።
እንዲህ ብለዋል: -

«የአላህ መልክተኛ [ﷺ] መዲና ሲገቡ ሰዎች በጥድፊያ ወደርሳቸው መጡ። እኔም ወደርሳቸው ከመጡት መሀል አንዱ ነበርኩ። ፊታቸውን አስተዋልኩት፤ አስተነተንኩት፤ በጥሞና አየሁት። ከዚያም ፊታቸው የሀሰተኛ ሰው ፊት እንዳልሆነ አወቅሁ። ከርሳቸው የሰማሁት የመጀመሪያው ቃል ተከታዩ ነው: -
«ሰዎች ሆይ: ሰላምታን አብዙ። ምግብን አብሉ። ዝምድናን ቀጥሉ። ሰዎች በተኙበት በሌሊት ስገዱ። ጀነት በሰላም ትገባላችሁ።» ቲርሚዚ ዘግበውታል።

የዐብዱላህ ኢብኑ ረዋሓ ቅኔም ይህንን ያስረዳል: -
لو لم تكن فيه آيات مبينة**كانت بديهته تنبيك بالخبر

«ተዓምር ባይኖረው እርሱነቱን ገላጭ
ፊቱ ይበቃዋል፤ ሐቅን ለሚፈልግ እውነት አረጋጋጭ።»

ከዓኢሻ [ረዲየላሁ ዐንሃ] የተዘገበው ደግሞ እንዲህ ነው: -
«የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ወደር-የለሽ ቆንጆ ነበሩ፤ አንፀባራቂ መልክ ነበራቸው። የገለጿቸው ሁሉ በበድር ጨረቃ መስለዋቸዋል። ላባቸው በፊታቸው ላይ ሲወርድ ሉል የሚንከባለልበት ይመስላል። ከምርጥ ሚስክ በላይ የሚያውድ መዓዛም ነበራቸው።»

የአጎታቸው አቡጧሊብ ገለፃ ይህን ያረጋግጣል: -
وأبيض يستسقى الغمام بوجهه**ثمال اليتامى عصمة للأرامل

«ነጭ ነው ሙሐመድ፤ የሚያበራ ፀሀይ፤
በፊቱ ከበጃ ዳመናን የሚጠራ፣ ከደረቀው ሰማይ፤

ረዳት ለሌለው ለየቲም መጠጊያ፤
ጋለሞታ አክባሪ፤ ከችግር መሸሸጊያ»

ኢብኑ ዐሳኪር፣ አቡ ኑዐይም እና አል-ኸጢብ "ሐሰን" የሚሰኝ ከፍ ያለ ደረጃ ባለው ዘገባ እንዳሰፈሩት እመቤታችን ዓኢሻ [ረዲየላሁ ዐንሃ] እንዲህ ብለዋል: - «እኔ ተቀምጬ ጥጥ እየፈተልኩ ነበር። ነቢዩ [ﷺ] ደግሞ ጫማቸውን እየሰፉ ነው። ከዚያም ላባቸው በቅንጣቸው ላይ ተንጠባጠበ። ከላባቸው ላይም ብርሃን መወለድ ጀመረ። በጣም ደነገጥኩ። «ምን አስደነገጠሽ?» አሉኝ። ቅንጥዎ እያላበ ነው። ከላብዎ ደግሞ ብርሃን ሲወለድ አየሁ። የሁዘይሎች አለቃ ቢያዮት ተከታዩ ግጥሙ ለርስዎ እንደሆነ ያውቅ ነበር አልኳቸው: -
ومبرأ من كل غبر حيضة**وفساد مرضعة وداء مغيل
وإذا نظرت إلى أسرة وجهه**برقت بروق العارض المتهلل
«ከወር አበባ ቁራጭ ያልተፈጠረ፤
በጥቢው ጊዜ ላይ ሌላን አስከትሎ አብሮት ያልነበረ፤
አይተህ ብታስተውል፣ የፈካውን ፊቱን፣ ኑር የመሰለውን፤
ትመለከት ነበር፣ አብረቅራቂ ብርሃን፣ ገፁን የሞላውን።»

ኢብኑ አቢ ኸይሰማ በበኩላቸው ተከታዩን ብለዋል: -
«የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ቅንጠ-ሰፊ ናቸው። ቅንጣቸው ከፀጉር መሀል ሲታይ፣ በንጋት ጨለማ ውስጥ የሚፈለቀቅ ብርቅታ ይመስላል። በሌሊት ፅልመት ውስጥ ግንባራቸው ሲወግግ፣ ፊታቸው ሰዎች ዘንድ ሲወጣ፣ ቅንጣቸው የሚንቦገቦግ ፋኑስ፣ የሚያንፀባርቅ ማሾ ይመስላል።
ገጣሚያቸው ሐስ-ሳን ኢብኑ ሳቢት እንደገለጻቸው ናቸው: -
*متى يبد في الليل البهيم جبينه
يلوح مثل مصباح الدجى المتوقد
*فمن كان أو من يكون كأحمد
نظام لحق أو نكال لملحد
«በድቅድቅ ጨለማ የሚያበራው ፊቱ ሲወግግ፤
የምሽት ቀንዲል የሚንቦገቦግ በሁሉ የሚፈለግ፤
እንደ አሕመድ ያለ መቼ ተፈጠረ መቼስ ሰው ነበረ፤
የእውነት መዘውር፤ ለክህደት ዱላ ከቶ ያልተሰበረ።»

ኑሩ ሙሐመድ
(ክፍል አራት)
==========
ሚስኩ ጦይባ
(የመዲናው ሽታ)
==========
ሽቶ ባይቀቡ እንኳን መዓዛቸው ማራኪ ነው። እንደውም የሰራ አካላቸው የሽቶዎች ዋና ነበር፤ ከሚስክ የላቀ መዓዛ ነበረው።

በእርግጥ ሽቶ ይወዳሉ። ሽቶ መቀባት ሱና መሆኑን ለኛ ለማስተማር ብዙ ጊዜ ሽቶ ይጠቀማሉ። በቲርሚዚይ ዘገባ እንደተነገረውም ተፈቃሪያችን [ﷺ] እንዲህ ብለዋል: - «ከዱንያችሁ ሽቶ እና ሴቶች እኔ ዘንድ ተወዳጅ ሆኑ። ሶላት የዓይኔ ማረፊያ ተደረገልኝ።»

ማራኪው ሽታቸው ተፈጥሮኣዊ ነው። መዓዛቸው ከሽቶዎች በላይ የሚማርክ፣ ከሚስክና ከዐንበር የበለጠ የሚናፈቅ እርካታ ነበረው።

ይህንን የሚያስረዱ ምስክሮች ልጥራ፤ ከቅርብ አገልጋያቸው ከአነስ ኢብኑ ማሊክ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እጀምራለሁ። እንዲህ ይላል: - «ከረሱል [ﷺ] ሽታ በላይ የሚማርክ ዐንበርም ሆነ ሚስክን ወይም ሌላ ሽቶን አላሸተትኩም። ከረሱል [ﷺ] በላይ ለስላሳ አካል ያለው የሐር ዓይነትም አልዳሰስኩም።» ቡኻሪ፣ ሙስሊም እና ሌሎችም ዘግበውታል። በቲርሚዚይ ዘገባ ላይ አነስ [ረዲየላሁ ዐንሁ] ተከታዩን ብለዋል: - «ከረሱል [ﷺ] የላብ ሽታ የበለጠ ማራኪ ሚስክም ሆነ ሌላ ሽቶን አሸትቼ አላውቅም።»

አሁንም አነስ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንደሚከተለው ይገልጿቸዋል: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] መልካቸው የፈካ ነበር። ላባቸው እንደ ሉል አንፀባራቂ ነው። ሲራመዱ የሚንደባለሉ ይመስላል (እርምጃቸው አጭር ነበር።)። ከርሳቸው መዳፍ በላይ የሚለሰልስ ምንም ዓይነት የሐር ጨርቅ አልዳሰስኩም። ከርሳቸው ሽታ የበለጠ የሚማርክ ሚስክም ሆነ ዐንበር አላሸተትኩም።» ሙስሊም ዘግበውታል።

አቡ ኑዐይም እና አል-ኸጢብ እንደዘገቡት: -

«እናታቸው አሚና ሲወልዷቸው ያዩትን እንዲህ ገልፀዋል: - «...ከዚያም ተመለከትኩት። የበድር ጨረቃን ይመስላል። ሽታውም እንደተቀመመ ሚስክ ነበር።»

ጃቢር ኢብኑ ሰሙራ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንዲህ ይላሉ: - «ከአላህ መልክተኛ [ﷺ] ጋር የዙህርን ሶላት ሰገድኩኝና ወደቤታቸው ሲሄዱ አብሬያቸው ወጣሁ። ሁለት ህፃናት መንገድ ላይ አገኟቸው። ተራ በተራ የአላህ መልክተኛ [ﷺ] የህፃናቱን ጉንጭ ዳበሱ።»...
ጃቢር እንዲህ ይላሉ: - «እኔንም ጉንጬን ዳበሱኝ። የእጃቸው ቅዝቃዜ ተሰማኝ፤ ሽታውም ከሽቶ ነጋዴ እንስራ የወጣ ይመስል ነበር።» ሙስሊም ዘግበውታል።

ኢማም አሕመድ አቡ ጁሐይፋን በመጥቀስ እንደዘገቡት: -
«ነቢዩ [ﷺ] ዉዱእ አድርገው የዙህርን ሶላት ሰገዱ። ከዚያም ሰዎች ተነስተው እጃቸውን እየያዙ ፊታቸውን መዳበስ ጀመሩ። አቡ ጁሐይፋ እንዲህ ይላሉ: - «እጃቸውን ይዤ ፊቴን ዳበስኩበት። ከበረዶ የላቀ ቅዝቃዜና ከሚስክ ይበልጥ የሚማርክ ሽታ ነበረው።»

ሶሐቦቻቸው ላባቸውን እንደ ሽቶ ይጠቀሙት ነበር። በረከቱን ከጅለው አካላቸውን ይዳብሱበት ነበር።...

ኢማም ሙስሊም ከአነስ [ረዲየላሁ ዐንሁ] ይዘው እንዳወሩት: - «ነቢዩ [ﷺ] ኡሙ ሱለይም ቤት እርሷ በሌለችበት በፍራሿ ላይ ይተኙ ነበር።... አንድ ቀን እቤት መጡና በፍራሿ ላይ ተኙ። ሰዎችም እርሷ ዘንድ ሄደው «ነቢዩ [ﷺ] ቤትሽ መጥተው ፍራሽሽ ላይ ተኝተዋል።» በማለት ነገሯት። ወደቤት መጣች። ነቢዩ [ﷺ] አልቧቸዋል። ላባቸውም ፍራሹ ላይ በተዘረጋ ቆዳ ላይ ተጠራቅሟል። ኡሙ ሱለይም ከሳጥኗ ብልቃጥ አወጣችና ላባቸውን ብልቃጥ ላይ መጭመቅ ጀመረች። ነቢዩ [ﷺ] ደነግጠው ተነሱ። እርሷም «የአላህ መልክተኛ ሆይ በረካውን ለህፃናቶቻችን ፈልገነው ነው።» አለች። እርሳቸውም «ጥሩ አድርገሻል!» አሉ።»

ሙስሊም እና አሕመድ አነስን [ረዲየላሁ ዐንሁ] ዋቢ በማድረግ ከኡሙ ሱለይም [ረዲየላሁ ዐንሃ] እንደዘገቡት: - «ነቢዩ [ﷺ] እርሷ ዘንድ እየመጡ

የረፋድ እንቅልፍ ይተኙ ነበር። የሚተኙበትን ምንጣፍ ኡሙ ሱለይም ታነጥፍላቸው ነበር። ነቢዩ [ﷺ] ላብ ይበዛባቸዋል። እርሷም ላባቸውን ሰብስባ በሽቶ ብልቃጥ ውስጥ ታጠራቅማለች። ነቢዩ [ﷺ] «ይህንን ለምን ታደርጊያለሽ?» ሲሏት «በላቦት ሽቶዬን እበርዛለሁ።» በማለት ትመልሳለች። እርሳቸውም ዱዓ ያደርጉላታል።»

የዑትባ ኢብኑ ፈርቀድ አስ-ሱለሚይ ሚስት -ኡሙ ዓሲም- እንዲህ ትላለች: - «በዑትባ ስር አራት ሚስቶች ነበርን። ሁላችንም ከአንዳችን ለመብለጥ ሽቶ በመምረጥ ላይ ትጉህ ነበርን። ዑትባ ደግሞ አልፎ አልፎ ጺሙን ቅባት ሲቀባ ከሚያስነካው ሽቶ በቀር ሌላ ሽቶ አይነካም። ነገርግን ከእኛ በላይ የእርሱ መዓዛ ልዩ ነው። ወደ ውጪ ሲወጣም ሰዎች «ከዑትባ ሽታ የበለጠ ማራኪ ሽታ አናውቅም።» ይሉታል። ከዚያም አንድ ቀን ጠየቅኩ: - «እኛ ጥሩ ለመሽተት እንለፋለን። ነገርግን አንተ ከኛ የበለጠ መልካም መዓዛ አለህ። ይህ ከየት የመጣ ነው?» አልኩት።
ዑትባ እንዲህ አለ: - «በረሱል [ﷺ] የእከክ በሽታ ገጠመኝና እርሳቸው ዘንድ በመምጣት ስሞታ

አቀረብኩ። ልብሴን እንዳወልቅ አዘዙኝ። አወለቅኩት። ከሀፍረተ ገላዬ ውጪ ሌላውን ሁሉ አውልቄ ፊትለፊታቸው ተቀመጥኩ። የአላህ መልክተኛ [ﷺ] እጃቸው ላይ ተፉና ጀርባዬን እና ሆዴን ዳበሱ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ሽታ አካሌ ላይ ተጣብቆ ቀረ።»

አቡ የዕላ እና ጦበራኒይ አቡሁረይራን [ረዲየላሁ ዐንሁ] በመጥቀስ በዘገቡት ሐዲስ ላይ አንድ ሰው ሴት ልጁን የሚሞሸርበት ሽቶ አጣ። የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ብልቃጥ አስመጡና ከላባቸው ላይ አጥልለው ሰጡት። «ይህንን እንድትጠቀም ንገራት።» አሉት። ሴትየዋ ይህንን ስትጠቀም የመዲና ሰዎች በሙሉ የሽቶዋ መዓዛ ይደርሳቸው ነበር። በዚህ የተነሳም ቤተሰቡ በሙሉ "ባለሽቶዎቹ ቤት" ተብለው መወሳት ጀመሩ።»
"ፈትሑል-ባሪ" ላይ ይህ ታሪክ ተወስቷል።...

መዓዛቸው የነካቸው ሰው ላይ ይላከካል። አብሮት ሊኖር ይጣበቅበታል። በነኩት ነገር ላይ፣ ባለፉበት መንገድ ላይ ይስተዋላል።
ጦበራኒይ እና በይሀቂይ ከዋኢል [ረዲየላሁ ዐንሁ]

እንደዘገቡት እንዲህ ብለዋል:- «የአላህ መልክተኛን [ﷺ] በጨበጥኩ ወይም አካላቸው አካሌን በነካ ቁጥር በእጄ ላይ መዓዛቸውን አገኘው ነበር። ሽታቸው ከሚስክ የበለጠ ማራኪ ነበር።»

ከዓኢሻ [ረዲየላሁ ዐንሃ] ተከታዩ ተዘግቧል: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] መዳፍ ከሐር የበለጠ ለስላሳ ነበር። ሽቶ ቢነኩም ባይነኩም መዳፋቸው የሽቶ ነጋዴ መዳፍ ይመስላል። የሚጨብጣቸውን ሰው ይጨብጣሉ፤ ከዚያም ቀኑን በሙሉ በመዓዛው ሲማረክ ይውላል። በህፃን ልጅ ጭንቅላት ላይ መዳፋቸውን ያሳርፋሉ፤ ከዚያም ጭንቅላቱ በህፃናት መሀል በመልካም መዓዛው የተለየ ይሆናል።» አቡ ኑዐይም እና በይሀቂይ ዘግበውታል።

ከአነስ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንደተዘገበው: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] በመዲና መንገድ ላይ ካለፉ መንገዱ በመዓዛቸው ይታወዳል። ሰዎችም «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] በዚህ በኩል አልፈዋል።» ይላሉ።» አቡ የዕላ እና በዝ-ዛር በሶሒሕ ሰነድ ዘግበውታል።
ከጃቢር ኢብኑ ዐብዲላህ እንደተዘገበው: - «የአላህ

መልክተኛ [ﷺ] ባለፉበት መንገድ የሚያልፍ ሰው በዚያ አቅጣጫ እርሳቸው እንዳለፉ በመልካም መዓዛው ያውቃል። በማንኛውም ድንጋይ በኩል ካለፉ ድንጋዩ ይሰግድላቸው ነበር።» ዳሪሚይ፣ በይሀቂይ እና አቡ ኑዐይም ዘግበውታል።

አል-ሙስነድ በተሰኘው የኢማም አሕመድ ጥንቅር ላይ ከዋኢል ኢብኑ ሑጅር እንደተዘገበው: - «ነቢዩ [ﷺ] ውሃ የተሞላ ባልዲ መጣላቸውና በጥቂቱ ተጎንጭተው መልሰው በባልዲው ውስጥ ተፉት። ከዚያም ባልዲው ውስጥ ያለውን ውሃ በጉድጓድ ውስጥ ጨመሩት። ከዚያ በኋላ ከጉድጓዱ ውስጥ የሚስክ ሽታ ይወጣ ጀመር።»

ኑሩ ሙሐመድ
(ክፍል አምስት)
==========
ምራቀ-ወርቅ
==========
ምራቃቸው አስደናቂ መለዮ አለው። የሰማዩ መልእክት ማረፊያ ሆነው ሲመረጡ ሁለመናቸው አብሮ እንደተመረጠ ያመለክታል። የኛ ነቢይ፣ ተፈቃሪው [ﷺ] ይህ ቀረሽ ያልሆነ ምልኣት ባለቤት፤ የቅድስና ምልክት፤ የንፅህና መባቻ ናቸው። ምራቃቸው ለታመመ ፈውስ፤ ለተጠማ መርኪያ፤ ለተራበ ጥጋብ እንደቸረ ታይቷል። በረከቱ፣ ፀጋው፣ ንፅህናው ዙርያውን አሳድጓል፤ የታደሉትን አልቋል። ጉዳይ ላለው ሁሉ ተዳርሷል።...
:
ስለቅዱሱ ምራቃቸው አንድ ሁለት እንበል።...
ታዲያ ወሬያችን ክብሩ ስለማይነጥፈው የልቅና ቂብላ ሲሆን ላለማወቃችን እያዘንን "አላሁ አዕለም!" እያልን ነው!...
:
«ዑመይራ ቢንት መስዑድ [ረዲየላሁ ዐንሃ] እና አምስት

እህቶቿ ቃል ሊጋቧቸው ነቢዩ [ﷺ] ዘንድ ገብተው ነበር። ቋንጣ እየበሉ አገኟቸው። አንድ የቋንጣ ቁራጭ አላመጡና ለሴቶቹ ሰጡ፤ ለዑመይራ ነው ያቀበሏት። ሁሉም በየተራ ይችን ቋንጣ አላመጡ። ዑመይራ በአላህ ምለው እንደሚናገሩት «ሁላቸውም መቼም ቢሆን መጥፎ የአፍ ጠረን ሳይገጥማቸው ወደ አኺራ ተሸኝተዋል።» ጦበራኒይ ዘግበውታል።

:

ስንት በሽተኛ በተቀደሰው ምራቃቸው ተባርኮ ወዲያው ሲፈወስ ታይቷል!...

ቡኻሪና ሙስሊም ከሰህል ኢብኑ ሰዕድ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንደዘገቡት: - «የኸይበር ቀን የአላህ መልክተኛ [ﷺ] እንዲህ አሉ: - «ይህንን ባንዲራ አላህ በእጁ [ኸይበርን] ለሚከፍትለት፣ አላህና መልክተኛውን ለሚወድ፣ አላህና መልክተኛው ለሚወዱት ሰው እሰጣለሁ።»

ሲነጋጋ ሰዎች የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ዘንድ ማልደው መጡ። ሁሉም ባንዲራው የሚሰጠው ሰው መሆንን ተመኝቷል። የአላህ መልክተኛ [ﷺ] «ዐሊይ ኢብኑ አቢጧሊብ የታለ?» አሉ።

«የአላህ መልክተኛ ሆይ! ዓይኑን ታሟል።» ተባለ።

የአላህ መልክተኛ [ﷺ] «መልእክት ላኩበት፤ ይምጣ!» አሉ።
እንዲመጣ ተደረገ። ዓይኑን ታሞ በሰው እየተመራ መጣ። ከዚያም የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ምራቃቸውን በዐይኖቹ ላይ ተፉበት። ወዲያው ዳነ። በሽታ የነበረበትም አይመስልም ነበር።»
:
ሌላም ታሪክ አለ። "ዘዋኢዱ ኢብኒ ሒብ-ባን" በተሰኘው መፅሀፍ ላይ ከዐብዱላህ ኢብኑ ቡረይዳ የተዘገበ። እንዲህ ሰፍሯል: -
«አባቴ እንዲህ ሲል ሰምቻለሁ: - «ዐምር ኢብኑ ሙዐዝ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እግሩ የተቆረጠ ቀን የአላህ መልክተኛ [ﷺ] እግሩ ላይ ተፉበትና ወዲያው ዳነ።»
ሪፋዐ ኢብኑ ራፊዕ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንዲህ ይላሉ: -
«የበድር ቀን በቀስት ተመታሁና ዐይኔ ፈሰሰ። የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ምራቃቸውን ተፉበትና ዱዓም አደረጉልኝ። ከዚያ በኋላ ዐይኔን አሞኝ አያውቅም።» ጦበራኒይ ዘግበውታል።
:
የዚድ ኢብኑ አቢ ዑበይድ እንዲህ ይላሉ: -
«የሰለማ [ረዲየላሁ ዐንሁ] ባት ላይ ጠባሳ አየሁ።

ከዚያም «የሙስሊም አባት ሆይ! ይህ ጠባሳ ምንድን ነው?» አልኳቸው። እንዲህ አሉኝ: - «ይች የኸይበር ጦርነት ቀን የተመታሁት ነበር። ሰዎች ሰለማ ከባድ አደጋ ደረሰበት አሉ። ነቢዩ [ﷺ] ሦስት ጊዜ ተፉበትና እስከ ዛሬ ድረስ አሞኝ አያውቅም።» ቡካሪ ዘግበውታል።

:

ከዐብዱረሕማን ኢብኑል-ሓሪስ፣ ዑበይዳን በመጥቀስ ከአያቱ እንደተዘገበው: - «የኡሑድ ጦርነት ጊዜ የአቡ ዘር ዓይን አደጋ ደረሰበት። ከዚያም ነቢዩ [ﷺ] ምራቃቸውን ተፉበት። ዓይኑም ካልተጎዳው ዓይን የበለጠ በጣም ጤናማው ሆነ።» አቡ የዕላ ዘግበውታል።

:

በይሀቂይ "ደላኢል" በተሰኘው መፅሀፋቸው ላይ እንደዘገቡት: - «ነቢዩ [ﷺ] በዓሹራ ቀን ከአቡ ኡሰይድ -ሰህል ኢብኑ ሰዕድ- [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንደተዘገበው የአላህ መልክተኛ [ﷺ] "ቡዷዓህ" የምትሰኘው የውሃ ጉድጓድ ዘንድ መጡና በባልዲ ቀድተው ዉዱእ አደረጉ። መልሰውም ባልዲው ውስጥ ከተቱትና ምራቃቸውን ተፉበት። በጉድጓዱ ውስጥም

ተፉ። ከዚህ ጊዜ በኋላ በህይወት ዘመናቸው ሁሉ አንድ ሰው በታመመ ቁጥር ሰዎች «በቡዷዐህ ውሃ እጠቡት።» ይላሉ። በውሃዋ ያጥቡታል፤ ከእስር እንደተለቀቀ ግመልም በጣም ንቁ ይሆናል።» ኢብኑ ሰዕድ ዘግበውታል።

... እጅግ በርካቶች በምራቃቸው በረከት ድነዋል። የአላህ ፀጋ በሆኑት ነቢይ ትልቁ የአላህን ፀጋ -ዓፊያን- ተጎናፀፈዋል። ምራቃቸው የፈፀመው ብዙ የፈውስ ጀብዶችም ተዘግበዋል፤ በሐዲስ ድርሳናት ውስጥ በሰፊው ተወስተዋል። ሌላ ቦታ እንፈልጋቸው!

:

በምራቃቸው በረከት የደረቀው ጉድጓድ ውሃ ማመንጨት ጀምሯል። ሰዉና እንስሳው ሁሉ የደረቀ አንጀቱን አርሷል።...

ከአነስ ኢብኑ ማሊክ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንደተዘገበው እንዲህ ብለዋል: - «ከአላህ መልክተኛ [ﷺ] ጋር "ቁባእ" መጥተን 'ቢእሩ-ገርስ' የተሰኘው የውሃ ጉድጓድ ዘንድ ደረሱ። ውሃ በአህያ ይጫንበት ነበር። ነገርግን ቀኑን በሙሉ ውለን ውሃ ማግኘት አቅቶን እንመለስ ነበር። የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ውሃ ተጎንጭተው ተጉመጠመጡና በባልዲ ላይ ተፉ። ከዚያም መልሰው

ጉድጓዱ ውስጥ ጨመሩት። ወዲያው ውሃዋ መንቧቧት ጀመረ።» ኢብኑ ሰዕድ ዘግበውታል።

:

ምራቃቸው እንደመብል ያገለገለበት አጋጣሚን እናንሳ።...

ረዚና እንዲህ ይላሉ: - «የአላህ መልክተኛ [ﷺ] የዓሹራን ቀን ያከብሩ ነበር። በእለቱ የሚጠቡ ህፃናትን ሰብስበው ዱዐ ያደርጉም ነበር። አፋቸው ላይ ይተፉና ለእናቶቻቸው «እስከሌሊት ድረስ ምንም አታጥቧቸው።» ይሉ ነበር። እንዳሉት ምራቃቸው ይበቃቸው ነበር።» አቡ የዕላ እና ጦበራኒይ ዘግበውታል።

:

ንፁሁ ምራቃቸው ስነምግባርንም ያፀዳል። የቆሸሸ ስብዕናን ያጥባል። የጨቀየን ስብዕና ይወለውላል። ተከታዩ እንይ...

ከአቡ ኡማማ [ረዲየላሁ ዐንሁ] እንደተዘገበው: - «በስድ ልሳኗ የምትታወቅ አንዲት ሴት መጣች። የአላህ መልክተኛ [ﷺ] ቋንጣ እየተመገቡ ነበር። አንዲት ቋንጣ አነሱና አፋቸው ውስጥ ከተቱ። አንዴ በቀኝ መልሰው በግራ ጉንጫቸው በተለያየ አቅጣጫ

ማላመጥ ጀመሩ።
ሴትየዋ እርሳቸው ዘንድ ቀረበችና «የአላህ ነቢይ ሆይ! አያበሉኝም?!» አለች።
«ኧረ አበላሻለሁ!» አሉና ከፊታቸው ያለውን አንስተው ሰጧት።
«እሱን አልፈልግም። በአፎት ውስጥ ያለውን ነው!» አለች። ከአፋቸው አውጥተው ሰጧት። አፏ ውስጥ ከተተችው። አብዝታ ካላመጠችው በኋላም ዋጠችው። ከዚህ ክስተት በኋላ ይች ሴት የነበረባትን መጥፎ ጠባይ ተወች። ስድ ምላሷ ተሰበሰበ።» ጦበራኒይ ዘግበውታል።
:
ነፍሴ ለዚህ ምራቅ ይሰዋ!
#ፊዳከ አቢ ወኡሚ #ያረሱለላህ!
https://t.me/fiqshafiyamh